# ደምብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ሠነዶች**: ACF, ACF-RA, BLB, COA, COA-RA, COA-RB, COB-RA, DJA-RA, IOE-RB, IOI-RA, JEE-RA, JGA-RC, KBA, KBA-RA

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት**: Office of Security and Compliance; Office of School Support and Improvement; Office of Special Education

## በተማሪዎች ሪፖርት ለሚደረጉ ጥቃቶች ምላሽ መስጠት

I. **አላማ**

አንድ ተማሪ ከማህበረሰብ ክስ ሲቀርብበ(ባ)ት ከትምህርት ፕሮግራሞች እና ከደህንነት ጋር የተያያዙ አስፈላጊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የአካባቢ ት/ቤት የሚወስዷቸውን እርምጃዎች በተመለከተ የሜሪላንድን ህግ ለመግለጽ እና ለመተግበር

II. **ትርጓሜ**

A. እስር፡ ማለት አንድ ሰው በህግ ጥበቃ ስር እንዲሆን ማለት ነው።

B. ማስወገድ፡ ማለት የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለው ውጤት ነው።

C. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ንብረት፡ ማለት ማንኛውም የ MCPS ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም፣ በ MCPS የተያዘ ወይም የሚተዳደር መሬት፣ የ MCPS አውቶቡሶች፣ ሌሎች የ MCPS መኪናዎች እና MCPS እንቅስቃሴ የሚያካሄድባቸው ቦታዎችን ጨምሮ ያሉ ንብረቶች ናቸው።

D. መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም፡ ማለት ጥቃቱ ሪፖርት በሚደረግበት ጊዜ ተማሪው(ዋ) MCPS ውስጥ የተመዘገበ(ች)ባቸው ኮርሶች፣ ትምህርቶች፣ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማለት ነው።

E. ሪፖርት የተደረገ ጥቃት፡ ማለት ከ MCPS ንብረት ውጪ የተፈፀመ እና በሜሪላንድ ህግ ኮድ (COMAR) 13A.08.01.17.A.(8)(c) ላይ የተገለጹ አንዳንድ የጥቃት ወንጀሎችን ያካተተ ማለት ነው። እነዚህ የአመጽ ወንጀሎች በዚህ ብቻ ባይወሰኑም የሚያካትቱት፥ ቤት ወይም ህንፃ ማቃጠል፣ጥቃት መፈፀም፣ ቤት ሰብሮ መዝረፍ፣ በወንጀለኛ ድርጅት ተግባር ላይ መሳተፍ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ንጥረ ነገሮች እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው አደንዛዥ እፅ ንጥረ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣ መሸጥ፣እና ማሠራጨት ጋር የተያያዙ ጥፋቶች፣ ጎጂ መሳሪያዎች እና የጦር መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣ እና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በመጠቀም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን አደገኛ እጾችና ንጥረ ነገሮችን ማምረት፣ማሠራጨት ወይም ማከፋፈል ናቸው።

III. **ጉዳዩ**

ሪፖርት በተደረገ ወንጀል ምክንያት መታሰር ማለት ከላይ በተገለጸው መሰረት ተማሪ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውጪ በተፈፀመ ጥቃት/ወንጀል ተጠርጥሮ(ራ) የተከሰሰ(ች) ከሆነ ነው። ስለዚህ፣ የተፈፀመው ወንጀል/ጥቃት የሚገልጸው ሪፖርት መደረጉን ብቻ ሣይሆን ጥቃቱ/ወንጀሉ የተፈፀመበትን ቦታ ጭምር ነው በቁጥጥር ስር ያዋለው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ቁጥጥር ስር ባዋለበት 24 ሰአት ውስጥ ወይም በተቻለ ፍጥነት ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ እና ለትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

ሪፖርት የተደረገ የወንጀል ድርጊት ብቻውን ተማሪን ከመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ለማገድ፣ ለማባረር፣ ወይም ለውጥ ለማድረግ ብቸኛ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል።

IV. **መረጃን ይፋ ማድረግ እና ምስጢራዊነት**

A. ስለ እስር መረጃ ወይም ማረጋገጫ መስጠት

1. የደህንነት እና ህግ ማስከበር ዋና ሃላፊ ከህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ሪፖርት የሚደረጉ ወንጀሎችን በተመለከተ መረጃ ለመቀበል እና የእስር መረጃዎችን (ማለትም፡ የተማሪው(ዋ)ን ስም፣ የተከሰተበት ቀን፣ እና ክሱን) ወዲያውኑ የማወቅና የማሳወቅ ኃላፊነት ያለበት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ ነው።

    a. ተማሪው(ዋ) ለሚማርበት/ለምትማርበት የ MCPS ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር እና ለሚመለከታቸው ቢሮዎች፣ ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ እና መሻሻል ቢሮ የሚመለከተው ዳይሬክተር (OSSI) እና የግንኙነት ዳይሬክተርን ጨምሮ፣ ወይም

    b. ተማሪው(ዋ) ለሚማርበት/ለምትማርበት ወይም ለሚዛወርበት/ለምትዛወርበት የሌላ ትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት።

    c. የታሰረ(ች)ው ተማሪ በ MCPS የህዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ፕሮግራም የተመዘገበ(ች) አካል ጉዳተኛ ተማሪ ከሆነ(ች)፣የደህንነት እና ደንብ ማስከበር ሃላፊው(ዋ) በቁጥጥር ስር የዋለ(ች)ውን ተማሪ መረጃ የህዝብ ላልሆነው ትምህርት ቤት ርእሰመምህር ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

2. ርእሰ መምህሩ ከደህንነት እና ህግ አስከባሪ ሀላፊ መረጃ ከመቀበላቸው በፊት ሪፖርት በተደረገው ጥፋት ምክንያት ስለተማሪው መታሰር መረጃ ከደረሰው የሚመለከተው OSSI ዳይሬክተር/ተወካይ ከደህንነት እና ደንብ የማስከበር ሃላፊ ጋር በመመካከር መረጃውን ያጣራል።

B. የእስር መረጃ ምስጢራዊነት

1. በሜሪላንድ ህግ ላይ እንደተገለፀው የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ያገኘው ሪፖርት የተደረገ የወንጀል ድርጊት መረጃ ሚስጥራዊ ነው (ማለትም፣ መረጃው ለህዝብ ይፋ አይደረግም)።

2. መረጃው መሰጠት ያለበት –

    a. ተማሪው(ዋ) ለተመዘገበ(ች)በት ወይም ለተዛወረ(ች)በት የሌላ ትምህርት ቤት ስርዓት ሱፐርኢንተንደንት፣ ወይም

    b. ፍርድ ቤት ባዘዘው መሠረት።

    c. በወጣት ጥፋተኞች ፍርድ ቤት ወይም በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ካልሆነ በቀር ወይም COMAR 13A.08.01.17.F ላይ ከተደነገገው ሁኔታ በስተቀር፣ ሪፖርት የተደረገው የወንጀል ድርጊት መረጃ ሚስጥራዊ በመሆኑ የፍርድ ቤት መጥሪያ ይፋ አይደረግም።

3. *መረጃው –*

   a. የዚህን ደንብ ዓላማ ለማስፈጸም ተማሪው(ዋ) ለተመዘገበበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ብቻ እንደአስፈላጊነቱ ይተላለፋል።

   b. ነገር ግን በተማሪው(ዋ) የትምህርት ማስረጃ ላይ በቋሚነት ተመዝግቦ መቀመጥ የለበትም፣እና

   c. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከተከናወነ መወገድ አለበት።

      i. ተማሪው(ዋ) ከተመረቀ(ች)፣

      ii. ተማሪው(ዋ) በቋሚነት ከትምህርት ቤት ከወጣ(ች)፣

      iii. የተማሪው(ዋ) ዕድሜ 22 ዓመት ሲሆን፣

      iv. ሪፖርት ከተደረገው ወንጀል ጋር የተያያዘው ጉዳይ ውድቅ ከተደረገ፣

      v. ተማሪው(ዋ) ሪፖርት በተደረገበ(ባ)ት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ካልተገኘ(ች)፣ ወይም

      vi. የተማሪው(ዋ) ጥፋት ሪፖርት ከተደረገው ወንጀል አነስተኛ መሆኑን የተማፀነ(ች) ከሆነ።

4. የደህንነት እና ደንብ የማስከበር ዋና ኃላፊ እና OSSI ዋና ኃላፊ የዚህን ደንብ አላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ሚስጥራዊ መረጃዎች ማግኘት ያለባቸው ተጨማሪ የ MCPS ሰራተኞችን በመለየት ፕሮቶኮል ያዘጋጃሉ።

5. ርእሰመምህሩ እና የሚመለከተው OSSI ዳይሬክተር ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ ወይም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ስለሚደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች ከኮሚዩኒኬሽንስ ዳይሬክተር/ተወካይ ጋር መነጋገር አለባቸው።

## V. አግባብ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም እቅድ ያዘጋጁ

MCPS ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪ ሪፖርት የተደረገ ወንጀል ጥቆማ ሲደርሰው 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ ተገቢ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት። እቅዱን በማውጣትና በመተግበር ላይ የሚሳተፉ ቢሮዎች 10 የትምህርት ቀናት የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ በትብብር መስራት ይጠበቅባቸዋል።

### A. *ማረጋገጫ መፈለግ*

በቁጥጥር ስር መዋሉ(ሏ) ከታወቀ በኋላ፣ ርእሰመምህሩ በሚከተለው መልኩ ተገቢ መረጃ ይሰበስባል፦

1. ተማሪው(ዋ) በግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም 504 ፕላን እንዳለው ርእስ መምህሩ በፍጥነት ማረጋገጥ አለበት።

   a. የአካል ጉዳተኛ ተማሪን ከተማሪው(ዋ) መደበኛ ፕሮግራም ለማስወጣት ከታሰበ፣ MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪን ከትምህርት ቤት ማገድ እና

ማባረርሰክሽን IV.C ወይም V.C. ላይ በተገለጸው መሰረት ሪፖርት ከተደረገበት10 የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ስብሰባ መደረግ አለበት።

b. ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት፣ በማንኛዉም የማረጋገጫ ግምገማ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ/እንድትገኝ ይጋበዛል/ትጋበዛለች።

2. የትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር አግባብ ካላቸው ሰራተኞች ጋር በመመካከር ከትምህርት ቤቱ እና ከሌሎች ተማሪዎች እና ሰራተኞች ጋር ግንኙነት መኖሩን አጣርቶ ይወስናል፥ እንዲሁም የተማሪው(ዋ) አካባቢ መገኘት ለሌሎች ተማሪዎች እና ለሰራተኞች ደህንነት አደጋ የሚያመጣ መሆኑን ጭምር ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

   a. ርእሰ መምህሩ፥ ከ OSSI ዳይሬክተር እና አግባብነት ካላቸው OSSI ተወካዮች፣ ከደህንነት እና ሥርአት ማስከበር ዳይሬክተር፣ የተማሪ ፐርሶኔል እና የትምህርት ክትትል አገልግሎት ክፍል (DPPAS) ጋር በመነጋገር አስጊ ሁኔታዎችን መገምገም ይችላል።

   b. MCPS አስገድዶ በመድፈር ወይም ጾታዊ ጥቃት በመፈፀም ሪፖርት በተደረገ ወንጀል የታሰረ(ች) ተማሪን የጥቃቱ ሠለባ ከሆነ(ች) ተማሪ ጋር በአንድ ትምህርት ቤት እንዳይከታተል/እንዳትከታተል ወይም በተመሳሳይ የትምህርት ቤት አውቶብስ እንዳይጓዝ/እንዳትጓዝ መከልከል አለበት፥ ይህ አይነቱ እርምጃ መወሰድ ያለበት ጥቃት የደረሰባ(በ)ትን ተማሪ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ጉዳት እንዳያስከትል ደህንነትን ለመጠበቅ አስፈላጊ ከሆነ ነው።

3. ተማሪው(ዋ) በአስገድዶ መድፈር ወይም በጾታዊ ጥቃት ወንጀል ጥፋተኛ ከሆነ(ች) ወይም ከተፈረደበ(ባ)ት ከተጠቂ(ዋ)ው ተማሪ ጋር በተመሳሳይ ትምህርት ቤት መከታተል ወይም በተመሳሳይ የትምህርት ቤት አውቶቡስ መጓዝ አይችልም/አትችልም። MCPS ደንብ COA-RBበወሲብ ጥቃት የተመዘገቡ ወንጀለኞች MCPS ንብረት ላይ መገኘትበአስገድዶ መድፈር ወይም በፆታዊ ጥቃት ወንጀል ለተከሰሰ(ች) ወይም ተከሶ(ሳ) የተፈረደበ(ባ)ት ተማሪ በሜሪላንድ የወሲብ ጥቃት ወንጀል ስለመመዝገብ እና የትምህርት ፕሮግራም ስለማዘጋጀት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ያስቀምጣል።

B. ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች የደህንነት እቅድ ማዘጋጀት

1. ርእሰ መምህሩ ተማሪው(ዋ) የደህንነት ስጋት እንደሚያስከትል/እንደምታስከትል ካመነ፣ ወዲያውኑ – እቅድ ማዘጋጀት አለበት

   a. ለተማሪው(ዋ) መሰጠት ስላለባቸው ተገቢ የሆኑ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ እና

   b. ለሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሠላማዊ የትምህርት ቤት አውድ ስለማስጠበቅ።

2. ርእሰ መምህሩ የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ በእቅድ ዝግጅት ላይ እንዲሳተፍ እና ጠቃሚ መረጃ እንዲሰጡ መጠየቅ ይኖርበታል።

3. ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት፣ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ጋር በእቅድ ዝግጅቱ ላይ ለመወያየት በማንኛውም ስብሰባ ላይ እንዲሳተፍ ርእሰ መምህሩ መጋበዝ አለበት። ወላጅ/አሳዳጊ ጠበቃ ካመጡ፣ርእሰመምህሩ የህግ አማሪ እንዲሳተፍ የጀነራል ካውንስል/ተወካይ ቢሮ መጠየቅ አለበት።

C. ሊፈፀም የሚችልን ጉዳት ግምት ውስጥ ማስገባት

1. በሜሪላንድ ህግ "ጉዳት ለማድረስ የሚሰነዘር ዛቻ" ከ "ደህንነት ስጋት" ያነሰ ስለሆነ ተማሪ በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ዛቻ ካልሠነዘረ(ች) በስተቀር ከላይ በተገለጸው አይነት ከመደበኛ ፕሮግራም ሊወገድ አይችልም።

2. ተማሪ ከመደበኛ ፕሮግራም መወገድ ማለት፥ ተማሪው(ዋ) ከዚህ በኋላ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በተመዘገበ(ች)በት ኮርሶች፣ ትምህርቶች፣ በተዛማጅ አገልግሎቶች፣ ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የመቀጠል እድል አይኖረውም/አይኖራትም ማለት ነው። አጠቃላይ ዝርዝሩን ባያመለክቱም የሚከተሉት ምሳሌዎች ተማሪ ከመደበኛ ፕሮግራም መወገድን የሚያመለክቱ ናቸው፡-

    a. በአካል ተገኝቶ ከመማር ወደ ቨርቹዋል ትምህርት መቀየር፣ ወይም

    b. ወደ አማራጭ ፕሮግራሞች አስተዳደራዊ ምደባ ማድረግ።

3. የሚከተሉት ምሳሌዎች ሙሉ ዝርዝር ባይሆኑም ተማሪው(ዋ) ሪፖርት የተደረገ ወንጀል ፈፀመ(ች) በተባለበት ወቅት ከሚወስደው/ከምትወስደው የመደበኛ ፕሮግራም ኮርሶች፣ ትምህርቶች፣ እና ከተዛማጅ አገልግሎቶች መባረር አይባልም፡-

    a. ተመሳሳይ ኮርሶችን፣ ትምህርቶችን፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችን፣ ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን በተለዋጭ የጊዜ ሰሌዳ የሚሰጥ ከሆነ፣ ወይም በተመሳሳይ ትምህርት ቤት መማር ከቀጠለ(ች)፣ ወይም

    b. ተመሳሳይ ኮርሶች፣ ትምህርቶች፣ ተዛማጅ አገልግሎቶች ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚሰጥ መርሃ ግብር ያለው ሌላ አጠቃላይ ትምህርት ቤት ከተመደበ(ች)።

4. ከላይ ሰክሽን V.A.2.a ላይ እንደተገለፀው የት/ቤቱ ርእሰመምህር ተማሪው(ዋ) በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል/እንደምትችል ካመነ እና ተማሪው(ዋ) ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም መወገድ ካለበ(ባ)ት ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ እንዲሰጥ ርእሰመምህሩ በጽሑፍ መጠየቅ አለበት። ይህንን ለመወሰን OSSI ኃላፊ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንትን ወክሎ ሊያገለግል ይችላል።

5. ለሱፐርኢንተንደንት የቀረበው ጥያቄ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

    a. ሪፖርት በተደረገ ጥፋት እና በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታ ማረጋገጥ።

    b. ከላይ በተገለጸው መሰረት ተማሪው(ዋ)ን ከመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ማስወገድን የሚስከትል በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ከባድ ጉዳት በሰነድ መያዝ።

    c. የሚመከር ተገቢ የትምህርት ፕሮግራም እና የደህንነት እቅድ።

    d. ርእሰ መምህሩ ተማሪው(ዋ) IEP ወይም 504 ፕላን ያለው/ያላት መሆኑን ማረጋገጥ። የፕሮግራም ለውጥ እንዲደረግ ለሱፐርኢንተንደንት የቀረበው ሃሳብ የተማሪው(ዋ)ን

የመደበኛ ፕሮግራም ለውጥ ካስከተለ፣ መግለጫ ወይም የምክንያቱ የሚገለፅበት ስብሰባ መደረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም፣ ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት ጠበቃው በስብሰባው ላይ እንዲገኝ የተጋበዘ መሆኑን በመግለጫ ወይም የግምገማ ሰነድ ላይ መመዝገብ አለበት።

e. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት የተማሪው(ዋ) ጠበቃ፣ በእቅድ አወጣጥ ላይ እንዲሳተፉ እና እቅዱን ለማዘጋጀት ጠቃሚ መረጃ እንዲያቀርቡ የተጋበዙበት ጥሪ በሰነድ ይቀመጣል።

3. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ –

a. ከተማሪው(ዋ)፣ ከተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት ከተማሪው(ዋ) ጠበቃ ጋር ኮንፈረንስ ማድረግ አለባቸው፤ እና

b. ተማሪው(ዋ) በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ስጋት መፈጠሩን መወሰን፣ ይህም ተማሪው(ዋ)ን ከመደበኛ ፕሮግራም እንዲወገድ ማድረግን ያስከትላል።

4. ከኮንፈረንሱ በኋላ፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ተማሪው(ዋ) ከመደበኛ የትምህርት ቤት ፕሮግራም መውጣት እንዳለበ(ባ)ት ከወሰነ፣ተማሪው(ዋ) ወይም የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ይግባኝ የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ከሚገለጽ ጽሑፍ ጋር ውሳኔው እንደደረሳቸው 15 ቀናት ውስጥ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

## VI. ይግባኝ

የይግባኝ ሂደቱ የሚከተሉትን COMAR 13A.08.01.17.D.(7)-(12) ድንጋጌዎች መከተል አለባቸው።

A. ለቦርድ የሚቀርበው ይግባኝ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንትን ውሳኔን አያስቆምም። ተማሪው(ዋ) በይግባኝ በሂደት ላይ እያለ(ች) በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በተወሰነው እቅድ ላይ በተገለጸው መሰረት የትምህርት መርሃ ግብሩን ይከታተላል/ትከታተላለች።

B. በህዝባዊ ችሎት እንዲታይ በተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ካልተጠየቀ በስተቀር ወይም ቦርዱ በችሎት እንዲገኙ አስፈላጊ ናቸው ብሎ ካላመነበት በስተቀር የሜሪላንድ ህግ እንደዚህ አይነት ጉዳዮች በዝግ ችሎት እንዲታዩ ይደነግጋል።

## VII. መስፈርቶችን መገምገም

ቢያንስ 45 የትምህርት ቀናት ውስጥ ከስቴቱ ዓቃቤ ህግ የሚተላለፈው ማሳወቂያ እንዳለ ሆኖ፥ ወይም ወዲያውኑ ከስቴቱ ዓቃቤ ህግ ሪፖርት የተደረገ ጥፋት መኖሩ ሲታወቅ የሚከተለው መደረግ አለበት፡-

A. የደህንነት እቅዱ፣ የትምህርት መርሃ ግብሩ፣ እና የተማሪው(ዋ)ን ሁኔታ መከለስ እና እንደአስፈላጊነቱ ማስተካከያዎች መደረግ አለባቸው።

B. ግምገማው ከተማሪው(ዋ) ወላጅ ግብአት ጋር ከላይ ሰክሽን V.A-B ላይ የተገለጹትን ግለሰቦች ያካትታል። ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት እቅዱን ለመገምገም የተማሪው(ዋ) ጠበቃ ከተማሪው(ዋ) ጋር ወይም ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ጋር በማንኛውም ስብሰባ ላይ አብሮ እንዲሳተፍ ይጋበዛል።

1. የግምገማው ውጤት ለተማሪው(ዋ) እና ለተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ በጽሁፍ መሰጠት አለበት።

2. ተማሪው(ዋ) ወይም የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ በግምገማው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ከላይ አንቀጽ VI ላይ በተገለጸው መሰረት ተማሪው(ዋ) ወይም የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

C. ሪፖርት የተደረገው ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ ወይም የወንጀለኝነት ውሳኔ የሚያሰጥ ከሆነ ወይም የወንጀል ክስ ወይም የጥፋተኝነት ክስ ለመመስረት በመጠባበቅ ላይ ያለ ከሆነ ፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ መረጃውን በሚስጥራዊነት ለሌላ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተማሪው(ዋ) በተመዘገበ(ች)በት ወይም በተዛወረ(ች)በት ስቴት ውስጥ ለሚገኝ ሌላ የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት የዚህን ደንብ ዓላማ ከማስፈፀም አንጻር፣ እና ለተማሪው(ዋ) የሚሰጠውን ማንኛውንም ትምህርታዊ ፕሮግራም ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች ጭምር መረጃ ውስጥ በማካተት በሚስጥር ፋይል ማስተላለፍ አለበት።

## VIII. *ሪፖርት የማቅረብ አስፈላጊነት/መስፈርቶች*

COMAR 13A.08.01.17.J ላይ በተገለፀው መሠረት MCPS የደረሰውን እያንዳንዱን የወንጀል ድርጊት መረጃ በየአመቱ ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ያቀርባል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ §7-303 እና 7-305፤ ANN CODE MD፣
የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ §§11-704፣ 11-704.1፣ 11-713፣ 11-721፣ እና 11-722፣
የሜሪላንድ ደንብ ኮድ (COMAR) 13A.08.01.17

**የደንቡ *ታሪክ*፡** አዲስ ደንብ ኖቬምበር 21, 2024

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
  (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
  (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
    (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
    (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
    (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
| --- | --- |
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
| --- |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024